ዉዱእን አሳምሮ አድርጎ ወደ ጁሙዓ በመምጣት ኹጥባን ዝም ብሎ ያዳመጠ በዚህኛው ጁሙዓና በቀጣዩ ጁሙዓ መካከል የሰራው ተጨማሪም ሶስት ቀን የሰራው ወንጀል ይማራል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ
(የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ዉዱእን አሳምሮ አድርጎ ወደ ጁሙዓ በመምጣት ኹጥባን ዝም ብሎ ያዳመጠ በዚህኛው ጁሙዓና በቀጣዩ ጁሙዓ መካከል የሰራው ተጨማሪም ሶስት ቀን የሰራው ወንጀል ይማራል። ጠጠርን የነካካ በርግጥም (የጁመዓውን ምንዳ) ውድቅ አድርጓል።"» [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እየነገሩን ያሉት: ዉዱእን ማዕዘናቶቹን አሟልቶ፣ ሱናዎቹንና ስነስርአቶቹንም በመፈፀም አሳምሮ ካደረገ በኃላ ወደ ጁሙዓ ሶላት በመምጣት ዝም ብሎ ኹጥባውን ያዳመጠና ከዛዛታ ነገር ዝም ያለ ሰው አላህ ለርሱ የአስር ቀን ትናንሽ ወንጀሎቹን ይምረዋል። እነሱም ከሰገደው ጁሙዓ ቀን እስከሚቀጥለው ጁሙዓ ድረስና የተጨማሪ ሶስት ቀን ወንጀል ነው። ምክንያቱም መልካም ስራ አስር አምሳያውን ያስመነዳልና። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ኹጥባ ላይ ለሚነገረው ተግሳፅ የልብን ትኩረት ከመንፈግ፣ በሰውነት ከመጫወት፣ ጠጠርን በመነካካትና በሌሎችም በሚጠምዱ የጨዋታ አይነቶች ከመዘናጋት አስጠነቀቁ። ይህንን የፈፀመ በርግጥም የጁሙዓውን የተሟላ ስራ ውድቅ አድርጎታል። ውድቅ ስራ የሰራ ሰውም ከተሟላ የጁሙዓ ምንዳ ለርሱ ድርሻ የለውም።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5433